የሰ/መ/ቁ. 55973

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** ወ/ሮ አፀደ ኤዶ ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ታደሠ - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ትኩ ዋቅሹም ጠበቃ አቶ ይመኑ ገብረፃድቅ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1987 ዓ.ም. እንደ ባልና ሚስት ስንኖር ያፈራናቸው የጋራ ሀብት አለ፡፡ ስለሆነም የጋራ ሀብቱን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት አሉ የሚሉትን ንብረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 6 ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ ንብረቶቹን በግሌ ያፈራኋቸው ናቸው፡፡ ከሣሽ /አመልካች/ የጋራ ንብረት ስለሆነ ያካፍለኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በሥር ተከሣሽ የሆኑት ተጠሪ ቀደም ሲል በፍ/ቤቱ ያቀረቡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ያልተካተተበትና ጐደሎ ስለሆነ መልሴን እንዳሻሽል ይፈቀድልኝ በማለት ህዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተከሣሽ /ተጠሪ/ መልሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸዋል፡፡ ተጠሪ /ተከሣሽ/ ታህሣስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ የተሻሻለ መልስ የከሣሽ /አመልካች/ የተከሣሽ /ተጠሪ/ ግንኙነት 1987 ዓ.ም. ተቋርጧል፡፡ ስለሆነም የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም የከሣሽ /አመልካች/ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽለው ባቀረቡት መልስ ላይ ያቀረቡትን የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ በመቀበል የከሣሽ /አመልካች/ የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ በአሥር ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የጋራ ንብረት እንዲያካፍለኝ ላቀረብኩት ክስ ተጠሪ በጽሑፍ ሙሉ መልስ ከሰጡና ግራ ቀኞችን የቃል ክርክርና ምስክሮች ተሰምተው ጉዳዩ ለውሣኔ ቀጠሮ ከተሰጠው በኂላ ተጠሪ መልሱን ለማሻሻል አቤቱታ አቀረበ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 መሠታዊ ድንጋጌ ከሚፈቅደው ውጭ ተጠሪ መልሱን እንዲያሻሽል የፈቀደ ሲሆን በተሻሻለው መልስ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ሆኖ መቅረብ የነበረበትን የይርጋ ክርክር አካትቶ አቀረበ፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኞችን ክርክር ከተጠናቀቀና ምስክሮች ከተሰሙ በኂላ ተጠሪ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጠው ብይን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244/1/ እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91/1/ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መልሴን ለማሻሻል ጥያቄ ያቀረብኩት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አካትቶ ለማቅረብ እንደሆነ ለሥር ፍ/ቤት ገልጩአለሁ፡፡ የሥር ፍ/ቤትም በዚሁ ጥያቄ አምኖበት መልሴን እንዳሻሽል ፈቅዶልኛል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ብይን የሰጠው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 17937 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በመከተል ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች የፈፀሙት የሕግ ስህተት የሌለ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ እንድሰናበት በማለት ታህሣስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም. የተጻፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ በማካተት መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ መፍቀዱና በተሻሻለው መልስ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ መሠረት አድርጎ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተከሣሽ የቀረበበትን ክስ ለመቃወም የሚችልበት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ለክሱ ከሚሰጠው ዝርዝር መልስ በፊት ወይም ከመከላከያ መልሱ ጋር ማቅረብ እንዳለበትና ፍ/ቤቱም በመጀመሪያ የክሱ መቃወሚያ ላይ ከሣሽ የሚሰጠውን መልስ በመቀበል ብይን መስጠት እንደሚገባው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ አንድ ጉዳይ በይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል የሚለው መከራከሪያ ተከሣሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት መቅረብ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተከሣሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርበው ይገባው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያ ሣያካትት የመከላከያ መልሱን ካቀረበ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት የይርጋ መከራከሪያውን እንደተወው የሚቆጠር መሆኑን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 ያጣመረ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያ ክስ የሚሰማው ፍ/ቤት ተከሣሽ የመከላከያ መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የሚፈቅደው ተከሣሽ መልሱን አሻሽሎ ማቅረቡ ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው (Necessary for the Purpose of the Real Question in Dispute) መሆኑ በፍታብሔር ሥነ-

ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 ተከሣሽ በፍትብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ድንጋጌዎች መሠረት በመጀመሪያ የክስ መቃወሚያነት ያላቀረበውን በተለይም በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ መሠረት ማቅረብ የሚባውንና የተወውን የይርጋ ጊዜ ገደብ መከራከሪያ አካትቶ እንዲያቀርብ የሚፈቅድ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ድንጋጌው ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ የክሱ ወይም የመከላከያ መልሱ መሻሻል በክርክር የተያዘውን ጉዳይ ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ ባልተገኘበት ሁኔታ ፍ/ቤት ክስ ወይም መልስ እንዲሻሻል መፍቀድ የሌለበት መሆኑን የሚያስቀምጥ ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ የጽሑፍና የቃል ክርክር ካደረጉና ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸውን አቅርበው ካሰሙ በኋላ ተጠሪ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርብ ይገባው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያ አካትቶ ለማቅረብ የመከላከያ መልሱን ለማሻሻል የቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎ ተጠሪ የመከላከያ መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የሰጠው ትዕዛዝ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው የመከላከያ መልስ ውስጥ በማካተት ያቀረበውን የይርጋ መከራከሪያና የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል የሰጠው ትዕዛዝ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244/3/ ንዑስ አንቀጽ 2 የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የዘረዘርነው የሕግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በይግባኝ አይቶ ማረም ሲገባው የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ የከፍተኛው ፍ/ቤት ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ ቀሪ እንደማይሆን በመገንዘብ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ